# የስደተኞች የግል ስፖንሰርሽፕ

## ዘመዶችን ስፖንሰር ማድረግ

**ደረጃ አንድ** — ብቁነት እና የቡድን ምስረታ
- የስፖንሰሩና የአመልካቹ ብቁነት ግምገማ



**ደረጃ ሁለት** — ሰነዶች እና ቅጾች
- የተሞሉ ሰነዶችን
- ለ IRCC ያስገቡ



**ደረጃ ሶስት** — መጪዎችና የመጀመሪያ ወራቶች
- ጅምር እና ወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍ
- ማረፊያ



**ደረጃ አራት** — በመካሄድ ላይ ያሉ ሀላፊነቶች እና የስፖንሰርሽፕ መጨረሻ
- ክትትል
- የስፖንሰርሽፕ መጨረሻ



ደረጃ አንድ

## ብቁነት እና የቡድን ምስረታ

Q. ስፖንሰር ለማድረግ የምፈልጋቸው ዘመዶች በተለያዩ አገሮች ውስጥ ናቸው፤ እናት እና ልጆች በትውልድ አገራቸው አያሉ አባትየው ግን በሰው አገር ጥገኝነት እየጠየቀ ነቸው።አባትየውን ብቻ ስፖንሰር ማድረግ እችላለሁ?

A. አዎ፤ ሁሉንም የትዳር አጋርን እና ከ ሃያሁለት አመት በታች የሆኑትን ጥገኞች በሙሉ በአንድ ማመልከቻ ላይ መካተትአለባቸው።

Q. በባህር ማዶ ያሉ ስደተኞች ስፖንሰር እንድናደርጋቸው የተወሰነ ገንዘብ ማዋጣት ይፈልጋሉ። ይህንን መቀበል እችላለሁ?

A. አይ፤ አይፈቀድም፤ ስፖንሰሮች ክሚረዷአቸው ስደተኞች ከመምጣታቸው በፊትም ሆነ ከደረሱ በሓላ በማናቸውም መንገድ ገንዘብ መቀበል የተከለከሉ ናቸው።

ደረጃ ሁለት

## ሰነዶች እና ቅጾች

Q. የስደተኞች ሰነዶች እና ቅጾች ለSAH እና ለቡድን አምስት ስፖንሰርሽፕ አንድ አይነት ናቸው?

A. አዎ፤ PIMM0008 አጠቃላይ ቅጽ፤ IMM5669 መርሀግብር A እና IMM0008 መርሀግብር 2 ለሁሉም የስደተኞች ስፖንሰርሽፕ መሞላት አለባቸው።

Q. ዋና አመልካች የስደተኛ ሁነታ ውሳኔ (RSD) ሰነድ እንዳለው እንዴት አውቃለሁ?

A. በአጠቃላይ፤ RSD የስደተኛ ሁኔታ ዉሳኔ /እውቅና ወይም የታወቀ ስደተኛ የሚሉትን ቃላት በግልጽ ያስቀምጣል። የጥገኝነት ጠያቂ ሰርተፊኬት ወይም የስደተኛ ምዝገባ የሚገልጹ ሰነዶች RSDS አይደሉም። እርግጠኛ ለመሆን፤ እባክዎ ለማረጋገጥ የስደተኞች ስፖንሰርሺፕ ስልጠና ፕሮግራምን ያነጋግሩ።

ደረጃ ሶስት

## ስለ መምጣትና የመጀመሪያ ወራት

Q. ጥያቄ፤ እኛ ስፖንሰር እያደረግን ያለው ቤተሰብ በቅርቡ ሊመጣ ነው፤ ነገር ግን መኖሪያ ማግኘት አልቻልንም። ከቡድናችን አባላት አንዱ በአሁኑ ግዜ እየተከራየ ያለው ቤዝመንት ስዊት አለው። ስለዚህ ለሚመጡት ስደተኞች እንዲሆን ብናደርግ ይቻላል?

A. በመጀመሪያ በአርስዎ ግዛት ውስጥ ያሉትን የተከራይና አከራይ ህጎች መገምገም አለቦት ። በአብዛኛዎቹ አውራጃዎች አከራይ ተከራይን ስፖንሰር ለተደረጉ ስደተኞች በቱን ለመከራየት አላማ ማስወጣት አይችልም ። ሁለተኛ፤ ከአዲሶቹ መጤዎች ጋር መኖር የሚፈልጉበት ቦታ እንደሆነ ለማወቅ ማማከር አስፈላጊ ነው።

Q. የስፖንሰርሽፕ ስምምነትን ለመጀመሪያ ጊዜ ስፈርም በትርፍ መኝታ ቤቴ ውስጥ ነጻ መኖሪያ ለመስጠት አቅጄ ነበር፤ ነገር ግን በቅርቡ ልጅ ወለድኩ፤ እናም መኝታ በቱ አሁን የለም። ስፖንሰር ለማደርጋቸው ዘመዶቹ የራሳቸውን ቤት ለመክራየት በቂ በጀት የለንም ፤ ስለዚህ ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ?

A. በዚህ ምክንያት ምንም እንኳን መኖሪያ ቤት በአይነት ለማቅረብ ቢታሰብም ቢያንስ የመጠለያ አበል RAP መጠን ባጀት እንዲዘጋጅ ይመከራል። በዚህ ሁኔታ ቡድንዎ መጠነኛ የሆነ የመጠለያ ገንዘብ ከማሰባሰብ ውጪ ሌላ አማራጭ የለዉም፤ ምክንያቱም አዲስ ለሚመጡት ቤት መስጠት የቡድኑ ሀላፊነት ነው።

Q. እኔ ስፖንሰር ያደረኩት ሰው እዚህ ስትደርስ የሰባት ወር ነፍሰጡር ነበረች ። አስቀድሞም አልተነገረኝም፤ የኔ ቡድን ያዘጋጀው ገንዘብም ለአንድ ሰው ብቻ ነው። አዲስ ለተወለደው ህጻን ተጨማሪ ድጋፍ መስጠት አለብን?

A. አዎ፤ ወርሀዊ ድጋፉ የሚሰላው በቤተሰቡ ብዛት እና ስብጥር በሚደርሱበት ጊዜ እና በ አስራሁለት ወራት ስፖንሰርሺፕ እንጂ በማመልከቻው ጊዜ አይደለም።

ደረጃ አራት

## በመካሄድ ላይ ያሉ ሃላፊነቶችና የስፖንሰርሺፕ መጨረሻ።

Q. እኔ ስፖንሰር ያደረኩት የቤተሰብ አባል ወደ ሌላ ከተማ መሄድ ይፈልጋል፤ የተቀረው ቤተሰብ ግን መቆየት ይፍልጋል። አሁንም ለሁለቱም የቤተሰብ አባል የገንዘብ ድጋፍ የማድረግ ግዴታ አለብኝ?

A. ስፖንሰሮች ስለ እነዚህ ለውጦች ለ IRCC ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባቸው፤ እና እንደሁኔታው IRCC ከፊል የስፖንሰርሺፕ ሊሰጥ ይችላል። እንደዚህ ከሆነ እርሶ በዋናው የሰፈሩ ማህበረሰብ ውስጥ ለሚቆዩት አዲስ መጪዎች ብቻ የገንዘብ ድጋፍ የመስጠት ሀላፊነት ይወስዳሉ ማለት ነው።

Q. የስፖንሰርሺፕ አንድ አመቱ ሊያልቅ ተቃርቧል፤ አዲስ የመጡት ሰዎች ገና እንግሊዝኛ ቋንቋ እየተማሩ ነው፤ ስራም ገና አላገኙም። ስለዚህ አስራሁለት ወር ካለፈም በህላ እርዳታ ማድረጉን የመቀጠል ህላፊነት አለብኝ ማለት ነው?

A. አይ፤ የስፖንሰርሺፕ ጊዜው አስራሁለት ወር ሲያልቅ፤ እርስዎ የስፖንሰርሺፑን ህላፊነት ተወጡ ማለት ነው፤ ነገር ግን ጊዜው ሊያልቅ ሲቃረብ አዲስ መጪዎቹ ስራም ከሌላቸው፤ ለክልሉ ወይም ለአውራጃው እንዴት ማመልከት እንዳለባቸው መርዳትና ከክልሉ እርዳት እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

Q. የኔ የገንዘብ ገቢ ሁኔታ ተለውጧልና አዲስ ለመጡት ሰዎች መርዳት አልችልም፤ እና አሁን እየረዳኋቸው የነበሩትን ሰዎች ከክልሉ የገንዘብ እርዳታ እንዲያገኙ እንዳያመለክቱ ማበረታታት እችላለሁ?

A. አይ፤ የስፖንሰርሺፕ ቡድኑ ለአዲስ መጪ ስደተኞች ለአንድ አመት አስፈላጊውን የገንዘብም ሆነ ማንኛውንም እርዳታ የማቅረብ ግዴታ አለበት። ስለዚህ የስፖንሰርሺፕ አመቱ ሳያልቅ ክልሉን እርዳታ መጠየቅ አይቻልም። ለአዲስ መጪዎቹ አስፈላጊውን የገንዘብ እርዳታ ማድረግ ቡድኑ ካልቻለ፤ ለ IRCC ማሳወቅ ያኖርበታል። ይህ ከሆነ ደግሞ የስፖንሰርሺፑ ጉዳይ ሊበላሽና የወደፊት ሌላን ሰው የመርዳት እድሉን ቡድኑ ሊያጣ ይችላል።

Q. ስፖንሰር ያደረኩት ሰው የሙሉ ሰአት ስራ ስላገኘ በየወሩ የምትከፍለኝን ገንዘብ ማቆም ትችላለህ አለኝ፤ ስለዚህ በየወሩ የምሰጠውን ገንዘብ ማቆም እችላለሁ?

A. ስፖንሰሮች እንዲቀንሱ የሚፈቀድላቸው በሚከተለው መልኩ ብቻ ነው። አዲስ መጪዎች ከ 50 ፐርሰንት በላይ የ RAP ተመኖችን ካገኙ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዶላር፤ ስፖንሰሮች አንድ ዶላር መቀነስ ይችላሉ።

